# የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ፍትህ ቢሮ

| | | |
|---|---|---|
| ቁሊቶ፤ ቁጥር______<br>ሰኔ ___ 2018 ዓ.ም | በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል<br>ይቅርታ ቦርድ የወጣ | Qulito No_________<br>June____/2026 |

*መመሪያ ቁጥር ____/2018 ዓ.ም*

## *ለማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ፍትህ ቢሮ ይቅርታ ቦርድ የይቅርታ ተጠቃሚ ሕግ ታራሚዎች የሚያቀርቡት የይቅርታ ጥያቄ ምልመላና መረጣ አፈፃፀም መመሪያ*

ለክልሉ ይቅርታ ቦርድ የሚቀርቡ የይቅርታ ጥያቄዎችን ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማስተናገድ እንዲቻል፣ የይቅርታ ጥያቄ የሚያቀርቡ አካላት ሊያሟሏቸው የሚገቡ ማስረጃዎችን በግልጽ ማስቀመጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የሕግ ታራሚዎችን የሚመለከት አስተያየት፣ መረጃ ወይም ምስክርነት ከሚሰጡ ተቋማትና ግለሰቦች የሚያስፈልገውን ዝርዝር በግልጽ ማስቀመጥ እና የቦርድ አባላት የይቅርታ አዋጁን እና ደንቡን በአግባቡ ለማስፈፀም የሚያስችላቸውን ስነ-ሥርዓት መደንገግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአዋጁን ዓላማ ለማሳካት የሚያስችል ግልጽ፣ ፍትሐዊና ወጥነት ያለው የይቅርታ ጥያቄ አቀራረብ እና ውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ እና ከዚህ አኳያ ነባሩ የክልሉ የይቅርታ ተጠቃሚ ሕግ ታራሚዎች ምልመላና መረጣ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 8/2008 የነበሩበትን ክፍተቶች በማስተካከል ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የክልሉ የይቅርታ ቦርድ በይቅርታ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ቁጥር 141/2008 አንቀጽ 16 መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1 አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የይቅርታ ተጠቃሚ ሕግ ታራሚዎች ምልመላና መረጣ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር _/2018" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2 ትርጓሜ

በክልሉ የይቅርታ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 157/2007 እና የይቅርታ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት ደንብ ቁጥር 141/2008 ትርጉም የተሰጣቸው በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላትና ሃረጎች በአዋጁና በደንቡ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

ሀ) "የመጨረሻ ዉሳኔ" ማለት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ባለዉ ፍርድ ቤት ዉሳኔ የተሰጠበት ሆኖ የይግባኝ ወይም የሰበር ክርክር የሌለበት ወይም ታይቶ እልባት ያገኘ ውሳኔ ነዉ፡፡

ለ) "የሕግ ታራሚ" ማለት በክልሉ ፍርድ ቤት በተከሰሰበት ወንጀል የመጨረሻ የቅጣት ውሣኔ አግኝቶ በክልሉ እና ከክልሉ ውጪ በሚገኝ ማረሚያ ተቋም ውስጥ ሆኖ የተወሰነበትን ቅጣት በመፈፀም ላይ የሚገኝ የሕግ ታራሚ ነው፡፡

ሐ) "ተበዳይ" ማለት የወንጀል ድርጊት ቀጥተኛ ሰለባ የሆነ ሰው ነው፡፡

መ) "የቅርብ ዘመድ" ማለት የይቅርታ ጥያቄ የሚቀርብለት የሕግ ታራሚ ወይም የተበዳይ ወላጅ ወይም አሳዲጊ፣ ለአካለ መጠን የደረሰ ልጅ ወይም የጉዲፈቻ ልጅ፣ የትዳር አጋር፣ እህት፣ ወንድም፣ አያት፣ አክስት ወይም አጎት ነዉ፡፡

ሠ) "ደጋጋሚ ወንጀል አድራጊ" ማለት በኢፌዴሪ የወንጀል ህግ መሰረት ወንጀል ፈጽሞ የተፈረደበትን የእስራት ቅጣት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ከፈፀመበት ወይም በይቅርታ ከቀረለት ቀን ጀምሮ በአምስት አመት ጊዜ ውስጥ ስድስት ወር እና ከዚያ በላይ እስራት በሚያስቀጣ አዲስ ወንጀል አስቦ በመፈፀም ጥፋተኛ የተባለ ሰው ነው፡፡

ረ) "የሀኪሞች ቦርድ" ማለት በመንግስት የሕክምና ተቋም ውስጥ በተለየ ወይም ውስብስብ በሆነ የህክምና ጉዳይ ለአንድ ታካሚ የተሻለና ፍትሃዊ ውሳኔ ለመስጠት ከተለያዩ የሕክምና ዘርፎች የተሰባሰቡ ስፔሻሊስት ሀኪሞች ስብስብ (ኮሚቴ) ነው፡፡

ሰ) "የሀኪሞች ቦርድ ምስክር ወረቀት (ሠርተፍኬት)" ማለት የሀኪሞች ቦርድ (ኮሚቴ) የአንድ ታካሚ የጤና ሁኔታ በጋራ መርምሮና ገምግሞ የሚሰጠው ይፋዊ እና ህጋዊ የህክምና

ማረጋገጫ ሠነድ ነው፡፡

ሽ) "መምሪያ ወይም ጽ/ቤት" ማለት እንደቅደም ተከተላቸው የዞን፣ የከተማ አስተዳደር፣ የወረዳ ወይም የልዩ ወረዳ ፍትህ ወይም ሰላምና ፀጥታ መምሪያ ወይም ጽ/ቤት ማለት ነው፡፡

**3 የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በክልሉ በሚገኙ ፍርድ ቤቶች በወንጀል ጉዳይ ጥፋተኛ ተብለው በክልሉ እየታረሙ በሚገኙ እና በዝውውር ከክልሉ ውጪ ሆነው የይቅርታ ጥያቄ በሚያቀርቡ ሕግ ታራሚዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የይቅርታ ጥያቄ አቀራረብ እና አሰጣጥ

**4 የይቅርታ ጥያቄ አቀራረብ**

ሀ) በአዋጁ፣ በደንቡ እና በዚህ መመሪያ የተቀመጡ መስፈርቶችን የሚያሟላ በክልሉ እና ከክልሉ ውጪ በሆነ ማረሚያ ቤት የሚገኝ ሕግ ታራሚ የይቅርታ ጥያቄውን በራሱ፣ በቅርብ ዘመዱ፣ በወኪሉ ወይም በጠበቃው በኩል ለክልል ይቅርታ ቦርድ ጽሕፈት ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

ለ) በአዋጁ አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የይቅርታ ጥያቄ ማቅረብ የሚችል ማንኛውም ሰው በአዋጁ አንቀጽ 16 ስር የተቀመጡ ይቅርታ የሚጠየቅለትን ታራሚ የሚመለከቱ መረጃዎችና ማስረጃዎች በግልጽ በሚያሳይ መልኩ የይቅርታ መጠየቂያ ቅጽ ላይ በመሙላት ማቅረብ አለበት፡፡

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (ለ) መሰረት የይቅርታ ጥያቄ የቀረበለትን ታራሚ በተመለከተ ታራሚው ከሚገኝበት ማረሚያ ቤት የታራሚውን ስነ-ምግባር በሚመለከት የተሰጠ አስተያየት፣ የሃኪሞች ቦርድ የህክምና ማስረጃ፣ እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 መሠረት የሚሰጡ ማስረጃዎች በደንቡ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 የተቋቋመው መልማይ ኮሚቴ በቃለ-ጉባኤ ተረጋግጦ ለቦርዱ ጽሕፈት ቤት መላክ አለበት፡፡

መ) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (ሀ) እንደተጠበቀ ሆኖ ፍትህ ቢሮ ወይም ይቅርታ ቦርድ ጽ/ቤት እና ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኮሚሽን በአዋጁ አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት በጥናት ላይ በመመስረት እንደአስፈላጊነቱ በማንኛውም ጊዜ ይቅርታ ሊደረግላቸው ይገባል የሚሏቸውን ታራሚዎች ለይተው ለቦርዱ የይቅርታ ጥያቄ ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡

ሠ) ፍትህ ቢሮ ወይም ይቅርታ ቦርድ ጽ/ቤት እና ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኮሚሽን

በአዋጁ አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት በጥናት ላይ በመመስረት እንደአስፈላጊነቱ በማንኛውም ጊዜ ይቅርታ ሊደረግላቸው ይገባል የሚላቸውን ታራሚዎች ዝርዝር በአዋጁ አንቀፅ 16 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ ከተገለፁት ማስረጃዎች ጋር በማያያዝ ለቦርዱ ያቀርባሉ፡፡

ረ) ማንኛውም የይቅርታ ጥያቄ በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ መሠረት ሊሚሉ የሚገባቸውን ማስረጃዎች አሟልቶ መቅረብ አለበት፡፡

## 5 ለይቅርታ አሰጣጡ መሟላት ያለባቸው መስፈርቶችና ከግምት ዉስጥ መግባት ያለባቸዉ ሁኔታዎች

1. የአዋጁ አንቀጽ 20 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የይቅርታ ጥያቄ ለማቅረብ የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፡-

   ሀ) የፈፀመውን የወንጀል ድርጊት አምኖ በመፀፀት የበደለውን ወገን እና ህብረተሰብ ለመካስ ያለው ዝግጁነት፤

   ለ) በማረሚያ ተቋም ቆይታው በተቋሙ ሲሰጡ የነበሩ ስልጠናዎችን እና ትምህርቶችን በመውሰድ ለመለወጥ የነበረው ፍላጎት፡፡

   ሐ) ደጋጋሚ ወንጀለኛ አለመሆን፤

   መ) በተቋሙ ውስጥ በምንም ዓይነት ጥፋት ተከሶ አለመቀጣቱ፤

   ሠ) የእድሜ ልክ ፍርደኛ ቅጣቱ ወደ25 ዓመት ዝቅ እንዲልለት 12 ዓመት ከ6 ወር መታሰሩን፤

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሐ) ድንጋጌ ቢኖርም ከሚከተሉት በአንዱ ወይም ከአንድ በላይ በሆነ ወንጀል ተከሶ የተፈረደበት ታራሚ የይቅርታ ጥያቄ ለማቅረብ የፍርዱን 1/2ኛ የእስር ጊዜ መፈፀም እና በእስር ቆይታው መልካም ስነ-ምግባር ያለው መሆን አለበት፡፡

   ሀ) በሕገ-ወጥ የጦር መሣሪያ ንግድ ወይም ዝውውር ወንጀል፤

   ለ) ከባድ የግድያ ወይም ከባድ የግድያ ሙከራ፤

   ሐ) ከባድ የአካል ጉዳት ወይም ከባድ የአካል ማጉደል ወንጀል፤

   መ) 5 ዓመትና በታች የሆነ ከባድ የውንብድና ወንጀል፣

   ሠ) በማንኛውም ፍርድ የሚገኝ የስርቆት ወይም የሌብነት ወንጀል፤

ረ) ከባድ የንብረት ማውደም ወይም የቤት ቃጠሎ ወንጀል፤

ሰ) ደን የመጨፍጨፍ ወንጀል፣ በሽታ ማሠራጨት ወንጀል፣ ቀላል እምነት ማጉደል፣ ማታለል እና ማጭበርበር ወንጀል (የሙስና ወንጀል ያልሆነ)፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ስር ከተጠቀሱት ወንጀሎች ውጪ ጥፋተኛ የተባሉ ወንጀሎች የይቅርታ ጥያቄ ለማቅረብ ከፍርዱ 1/3ኛ የፈፀሙ እና ጥሩ ስነ-ምግባር ያላቸው መሆኑ የተረጋገጠላቸው መሆን አለበት፡፡

4. በደንቡ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተዘረዘሩ ወንጀሎችን ሳይጨምር በሌሎች ወንጀሎች ጥፋተኛ የተባሉ ከሚከተሉት አንዱ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ሁኔታዎች ከተሟሉ የይቅርታ ጥያቄ ሊቀርብ ይችላል፡፡

   ሀ) እስከ ሶስት ዓመት የሚደርስ የእስራት ቅጣት የተፈረደባት እድሜዋ ከ50 ዓመት በላይ የሆነች ሴት ታራሚ ወይም እድሜው ከ55 ዓመት በላይ የሆነ ወንድ ታራሚ የፍርዱን 1/4ኛ መፈፀም፤

   ለ) እስከ ሶስት ዓመት የሚደርስ የእስራት ቅጣት የተፈረደበት እድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ የሕግ ታራሚ የፍርዱን 1/4ኛ መፈፀም፤

   ሐ) እስከ ሶስት ዓመት የሚደርስ የእስራት ቅጣት የተፈረደባት እድሜዉ ከሁለት ዓመት ያልበለጠ ህፃን ልጅ ይዛ ወደ ማረሚያ ቤት የገባች ወይም ነፍሰጡር የሆነች ታራሚ የፍርዱን 1/4ኛ መፈፀም፤

   መ) እስከ ሶስት ዓመት የሚደርስ እስራት የተፈረደበት አካል ጉዳተኛ ታራሚ የፍርዱን 1/4ኛ መፈፀም፤ ወይም

   ሠ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከፊደል ተራ (ሀ-መ) ከተጠቀሱት ከአንድ በላይ ሁኔታዎችን የሚያሟላ እስከ አምስት ዓመት የሚደርስ እስራት የተፈረደበት ታራሚ የፍርዱን 1/5ኛ መፈፀም፣ አለበት፡፡

**6 በልዩ ሁኔታ ስለሚቀርብ የይቅርታ ጥያቄ**

1. በደንቡ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2 እና የዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ድንጋጌ ቢኖርም ከሚከተሉት አንዱ ወይም ከአንድ በላይ ሁኔታዎች ከተሟሉ የይቅርታ ጥያቄ በልዩ ሁኔታ በማንኛውም ጊዜ ሊቀርብ ይችላል፡፡

   ሀ) እስከ አምስት ዓመት የሚደርስ እስራት የተፈረደበት ታራሚ ሆኖ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ዉጤት ካሟላ፤

   ለ) ታራሚው በከባድ በሽታ ተይዞ በማረሚያ ቤት ለመቆየት አስቸጋሪ መሆኑ

በሃኪሞች ቦርድ ከተረጋገጠ፤

ሐ) ከታራሚ ጋር አብሮ የሚኖር የታራሚ ልጅ የጤና ችግር ያጋጠመው በመሆኑ ምክንያት ለዕርምትና ለአያያዝ አስቸጋሪ ስለመሆኑ በሃኪሞች ቦርድ የተረጋገጠ ማስረጃ ከቀረበ፤

መ) ነፍሰጡር የሆነች ታራሚ ከእርግዝና ጋር በተያያዘ ከፍተኛ የጤና ችግር ያጋጠማት ስለመሆኑ በሃኪሞች ቦርድ የተረጋገጠ ማስረጃ ከቀረበ፣ ወይም

ሠ) የይቅርታ ጥያቄው መቅረብ ለትክክለኛ ፍትሕ አሰጣጥ እንደሚረዳ በቦርዱ ሰብሳቢ ታምኖበት ከቀረበ።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የይቅርታ ጥያቄ ሲቀርብ እንደወንጀሉ ሁኔታ ሌሎች በዚህ መመሪያ የተደነገጉ መስፈርቶች መሟላታቸው ሊታይ ይችላል።

## 7 የገንዘብ መቀጮ ስለመክፈል

በአዋጁ፣ በደንቡና እና በዚህ መመሪያ መሠረት የይቅርታ ጥያቄ ያቀረበ ታራሚ ይቅርታ በሚጠይቅበት ፍርድ ተጨማሪ የገንዘብ መቀጮ የተወሰነበት ከሆነ የተወሰነበትን የገንዘብ መቀጮ የከፈለ መሆኑን ወይም ለመክፈል አቅም የሌለው መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ አለበት።

## 8 እርቅ ስለሚፈፀምበትና ስለሚቀርብበት ሥርዓት

1. ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ወንጀሎችን ፈጽመው የተቀጡ ሕግ ታራሚዎች በይቅርታ ተጠቃሚ ለመሆን እርቅ መፈፀምና ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

ሀ) በየትኛውም ፍርድ የሚገኝ የግድያ ወንጀል፤

ለ) በየትኛውም ፍርድ የሚገኝ የግድያ ሙከራ ወንጀል፣

ሐ) 5 ዓመትና በላይ የተፈረደባቸው የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል፣ የአካል ማጉደል ወንጀል፤ የእሳት ቃጠሎ ወንጀል፣ የንብረት ማውደም ወንጀል።

2. የእርቅ ማስረጃዎች ከዚህ በታች በተዘረዘሩት መሥፈርቶች መሠረት ተፈጽመው ካልቀረቡ ተቀባይነት የላቸውም።

ሀ. በሕግ ታራሚው በራሱ ወይም በቤተሰቦቹ አማካይነት እርቅ ከተፈፀመ በኋላ መምሪያው ወይም ጽ/ቤቱ እርቅ መፈፀሙን እና የሠነዱን ትክክለኛነት በማረጋገጥ ሕግ ታራሚው ለሚገኝበት ማረሚያ ተቋም እንዲደርስ ያደርጋል።

ለ. ማረሚያ ተቋሙ እርቅ ለመፈፀም እየፈለጉ የሚያስፈጽምላቸው የሌላቸውን ሕግ ታራሚዎች በመለየት ለመምሪያው ወይም ለጽ/ቤቱ በደብዳቤ ያሳውቃል፤ መምሪያው ወይም ጽ/ቤቱ ሕግ ታራሚዎቹ የሚገኙበት ቀበሌ አስተዳደር የአካባቢ ሽማግሌዎች እርቁን እንዲያስፈጽሙና የደረሱበትን ውጤት እንዲያሳውቁ ያደርጋል፤ አፈፃፀሙም በዚህ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (ሀ) በተገለፀው መሠረት ይሆናል፡፡

ሐ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (ሀ) ሥር የተደነገገው ቢኖርም እርቅ ሲጠየቅ በተጎጂው ወይም በተጎጂው ቤተሰቦች የተጋነነ ከፍተኛ ገንዘብ ወይም ለህግ እና ከህብረተሰቡ ሞራል ተቃራኒ የሆነ ተግባር እንዲፈጽሙ ከተጠየቁ ወይም እርቅ ሊፈጽም የሚችል ተጎጂ ወይም የተጎጂው ቤተሰብ ከጠፋ ወይም ከሀገር ውጪ ከሆነ ይህንን ለማረጋገጥ ስልጣን የተሰጠው አካል ይህንኑ ካረጋገጠ እርቅ ሊፈፅሙ የማይችሉ ሕግ ታራሚዎች ተብለው የይቅርታ ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

መ. የይቅርታ ጥያቄ በሚቀርብበት ወቅት የዞኑ የሕግ ታራሚዎች የይቅርታ ጥያቄ መልማይ ኮሚቴ የሕግ ታራሚዎቹን ማህደር መርምሮ የይቅርታ መስፈርቱን የሚያሟሉ መሆኑን ሲያረጋግጥ ታራሚዎቹ ከሚያቀርቡት የይቅርታ ጥያቄ ማመልከቻ ቅጽ ጋር ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎችን የእርቅ ሠነድ፣ መቀጮ የተከፈለበትን ደረሰኝና ሌሎች ደጋፊ ሠነዶች ለይቅርታ ቦርድ ጽ/ቤት ያቀርባል፡፡

ሠ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ከ(ሀ-መ) የተዘረዘሩ ድንጋጌዎች ቢኖሩም በትራፊክ አደጋ ወንጀል ፈጽመው የሚገኙ ሕግ ታራሚዎችን በሚመለከት ወንጀሉ ሆን ተብሎ የተፈፀመ ካልሆነ በስተቀር በኢንሹራንስ ለተጎጂው ወይም ለተጎጂው ቤተሰብ የካሳ ክፍያ ስለመፈፀሙ የሚገልጽ የፍርድ ቤት ውሳኔ ወይም የኢንሹራንሱን ማስረጃ በማቅረብ እርቅ የመፈጸም ግዴታ ሳይኖርባቸው የይቅርታ ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ፡፡

3. የክልሉ ይቅርታ ቦርድ ጽ/ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የቀረበ ማስረጃ አጠራጣሪ ሆኖ ሲያገኘው ተበዳይን፣ የተበዳይን የቅርብ ዘመድ፣ የሟችን የቅርብ ዘመድ ወይም የእርቅ ማስረጃ የሰጠውን አካል በመጠየቅ ወይም በሌላ በተገቢ መንገድ የእርቁን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለበት፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 (ለ) መሠረት የሚቀርብ እርቅ ለመፈፀም የተደረገ ጥረት በቦርዱ ተቀባይነት የሚኖረው ይቅርታ ጠያቂው ከግል ተበዳይ ጋር ወይም ከሟች የቅርብ ዘመድ ጋር እርቅ ለመፈፀም ፍላጎት ቢኖረዉም የሚታረቀው አካል እንቢ ስለማለቱ ወይም የተጋነነ ካሳ ስለመጠየቁ በሚመለከተው አካል ተረጋግጦ ሲቀርብ ወይም በፍርድ ቤት የመጥፋት ውሳኔ የተሰጠበት ከሆነ ወይም ከሀገር የወጣ ከሆነ ስለመውጣቱ ከኢምግሬሽን እና የዜግነት ጉዳይ ማረጋገጫ ማቅረብ ከቻለ ወይም ቦርዱን የሚያሳምን ሌላ በቂ ምክንያት ሲኖር ነው፡፡

5. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ያታን ወይም እድሜን

መሠረት በማድረግ በሴቶች እና ህፃናት ላይ የተፈፀመ ወንጀል ከሆነ እርቅ ወይም የእርቅ ሙከራ ቢኖርም ቦርዱ የይቅርታ ጥያቄውን ልዩ ትኩረት በመስጠት የመመርመር ስልጣን አለው፡፡

6. በዚህ መመሪያ የተቀመጡ ሌሎች ቅድመ-ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ደንቡ በአንቀጽ 4 እንደደነገገው የሕግ ታራሚዎቹ መፈታት ለክልሉ ሰላም፣ ልማት እና ለሕግ የበላይነት መስፈን ጠቃሚና አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት በጎሳ ሽማግሌዎች የሚቀርቡ የእርቅ ሠነዶች ተቀባይነት አላቸው፡፡

## ፱ ከማረሚያ ቤት ስለሚቀርብ ማረጋገጫ

1. የይቅርታ ጥያቄ ሲቀርብ ሕግ ታራሚዎች በማረሚያ ተቋሙ ቆይታቸው የነበራቸውን የመታረም እና የመታነፅ ሂደት፣ የስነ-ምግባር መሻሻል፣ በቆይታቸው ያደረጉትን የሙያ ወይም ማህበራዊ ተሳትፎ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች በአግባቡ መፈተሽ አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ከማረሚያ ቤት የሚሰጠው ማረጋገጫ በማረሚያ ተቋሙ ኃላፊ ፊርማ ለቦርዱ ጽ/ቤት መላክ አለበት፡፡

## ፲ በቅድመ ሁኔታ ስለሚሰጥ ይቅርታ

1. የከፍተኛ ትምህርት ለመከታተል የሚያስችል ውጤት ያላቸው ታራሚዎች ትምህርታቸውን መከታተል እንዲችሉ፣ ልዩ ሙያ ያላቸው ታራሚዎች በሙያቸው እንዲያገለግሉ ወይም በሌሎች ተመሳሳይ ምክንያቶችን ቦርዱ በቅድመ ሁኔታ ላይ ተመስርቶ ይቅርታ እንዲሰጥ ለርዕሰ መስተዳደሩ የውሳኔ ሃሳብ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

2. ቦርዱ በቅድመ ሁኔታ የሚሰጠው ይቅርታ በጊዜ የተገደበ እና የይቅርታ ተጠቃሚው በጊዜ ገደቡ ውስጥ ማሟላት የሚገባውን ግዴታ በግልጽ ያስቀመጠ መሆን ይኖርበታል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ቦርዱ በሚሰጠው የይቅርታ ውሳኔ ላይ የይቅርታ ተጠቃሚው በተወሰነ ጊዜ ለጽህፈት ቤቱ በአካል ወይም በሚወሰን ሌላ አመቺ መንገድ ስለቅድመ ሁኔታው አፈጻጸም ሪፖርት እንዲያቀርብ ይወስናል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ቦርዱ ያስቀመጠውን ቅድመ ሁኔታ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ እስኪጠናቀቅ ክትትል ማድረግ የጽህፈት ቤቱ ኃላፊነት ነው፡፡

5. የይቅርታ ተጠቃሚው ይቅርታ ከተደረገለት በኋላ በ5 ዓመት ጊዜ ውስጥ በሌላ ታስቦ በተፈፀመ ወንጀል ተከሶ በፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተላለፈበት የተሰጠው ይቅርታ በማንኛውም ጊዜ እንዲሻር ወይም እንዲነሳ የዉሳኔ ሃሳብ ለርዕሰ መስተዳደሩ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት በቅድመ ሁኔታ የተሰጠውን ውሳኔ ተከታትሎ ማስፈጸም የክልሉ ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኮሚሽን ኃላፊነት ነው፡፡

7. ቦርዱ በዚህ አንቀጽ ከተጠቀሱት በተጨማሪ የህዝብ፣ የመንግስት እና የታራሚዎችን ጥቅም ባስጠበቀ መልኩ ሌሎች አስፈላጊ የሚላቸውን ቅድመ ሁኔታዎች በማስቀመጥ ይቅርታ እንዲሰጥ ለርዕሰ መስተዳደሩ የውሳኔ ሃሳብ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

## ፲፩ የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊነት

የቦርዱ ጽሕፈት ቤት በአዋጁ አንቀጽ 13 የተሰጡት ተግባርና ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ መመሪያ መሠረት የሚቀርብ የይቅርታ ጥያቄ ማመልከቻ ጋር ተያይዘው ሊቀርቡ የሚገባቸው ማስረጃዎችና የቀረቡት ዕጩ የይቅርታ ተጠቃሚ ሕግ ታራሚዎች የይቅርታ መሥፈርቱን አሟልተው መቅረባቸውን በማረጋገጥ ዝርዝር መረጃውን ከመግለጫ ጋር ለቦርዱ ያቀርባል፡፡

## ፲፪ የይቅርታ ጥያቄ ማመልከቻን ስለመመርመር እና የውሳኔ ሃሳብ ስለማቅረብ

ቦርዱ፡-

1. የቀረበለትን የይቅርታ ጥያቄ በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ የተቀመጡ መስፈርቶች ወይም ቅድመ-ሁኔታዎች መሟላታቸውን ይመረምራል፤ ያረጋግጣል፤

2. በዚህ መመሪያ መሠረት ተሟልቶ የቀረበለትን የይቅርታ ጥያቄ በመመርመር የይቅርታ ጥያቄውን ስለመቀበሉ ወይም አለመቀበሉ ይወስናል፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የይቅርታ ጥያቄውን ያልተቀበለው ወይም ውድቅ ያደረገው ከሆነ ጥያቄውን ያልተቀበለበትን ወይም ውድቅ ያደረገበትን ምክንያት በግልጽ በማስፈር ውሳኔውን በጽሕፈት ቤቱ በኩል የይቅርታ ጥያቄ ላቀረበው አካል እንዲደርሰው ያደርጋል፤

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የይቅርታ ጥያቄውን ከተቀበለው ወይም የይቅርታ መስፈርት የሚያሟላ መሆኑን ካመነበት ጥያቄውን የተቀበለበትን ምክንያት በዝርዝር በጽሁፍ በማስፈር የይቅርታ ውሳኔ ሃሳብ ለክልሉ ርዕሰ መስተዳደር

ይልካል፡፡

## ፲፫ የይቅርታ ዋጋ ማጣት

ቦርዱ በአዋጅ፣ በደንብ እና በዚህ መመሪያ መሠረት ይቅርታ እንዲደረግ የውሳኔ ሃሳብ የሰጠበትን የይቅርታ ጥያቄ በአዋጁ አንቀጽ 23 ላይ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ በሚከተሉት ምክንያቶች የተሰጠው የይቅርታ ወሳኔ በማንኛውም ጊዜ ዋጋ እንዲያጣ ለርዕሰ መስተዳደሩ የውሳኔ ሃሳብ ሊያቀርብ ይችላል፡-

1. የይቅርታ ውሳኔው ወይም የውሳኔ ሃሳቡ በስም ስህተት ወይም በማንኛውም ሌላ መሰረታዊ ስህተት ምክንያት ይቅርታ ሊደረግለት የማይገባ ታራሚ የይቅርታ ተጠቃሚ መሆኑን ሲያረጋግጥ፡፡
2. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 መሰረት በቅድመ ሁኔታ የተሰጠ የይቅርታ ጥያቄ ቅድመ ሁኔታው አለመሟላቱ ወይም አሳማኝ ባልሆነ ምክንያት ቅድመ ሁኔታዉ መጣሱ ሲያረጋግጥ፡፡

## ፲፬ ስህተትን ስለማረም

የቦርዱን የውሳኔ ሃሳብ ወይም የይቅርታ ውሳኔ መሰረታዊ ይዘት ሊለውጥ የማይችል የፊደል፣ የእድሜ፣ የፆታ፣ የአድራሻ ወይም መሰል ቀላል ስህተት መኖሩ ሲረጋገጥ ቦርዱ ድጋሜ ለውሳኔ መቀመጥ ሳያስፈልገው የቦርዱ ሰብሳቢ የተፈጠረውን ስህተት ማረም ይችላል፡፡

## ፲፭ የመተባበር ግዴታና ተጠያቂነት

1. ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘ የተሳሳተ መረጃ ያቀረበ ወይም የሰጠ ማንኛውም አካል ወይም ግለሰብ አግባብ ባለው ህግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡
2. በዚህ መመሪያ የተቀመጡትን ግዴታዎች ያልፈፀመ ወይም ለመፈፀም ያልተባበረ ማንኛውም አካል ወይም ግለሰብ አግባብ ባለው ህግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡
3. ማንኛውም ይህን መመሪያ የሚያስፈጽም አካል ስልጣኑን ያለአግባብ ተጠቅሞ ይቅርታ ማግኘት የሚገባቸውን የህግ ታራሚዎች የይቅርታ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ወይም ተጠቃሚ መሆን የማይገባቸውን እንዲጠቀሙ የረዳ፣ የተሰሳተ መረጃ የሰጠ አግባብ ባለው ህግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

### ፲፮ የተሻሩና ተፈፃሚት የሌላቸው ሕጎች

1. የክልሉ የይቅርታ ተጠቃሚ ሕግ ታራሚዎች ምልመላና መረጣ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 8/2008 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡
2. ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በተመለከተ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

### ፲፯ መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በቦርዱ ፀድቆ በፍትሕ ቢሮ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ቁሊቶ፤**

**ሰኔ፣ 2018 ዓ.ም**

**አክመል አህመዲን ሶማ**

**የፍትሕ ቢሮ ኃላፊ እና የክልሉ ይቅርታ ቦርድ ሰብሳቢ**